EthioLion

# <u>እንቅልፍ ለምኔ ?!</u>

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ጎጆዬ ሲቃጠል ደጄ ጨኸት ሞልቶ፤
አንድ ጣሳ ውሃ ይለግሰኝ ጠፍቶ፤
እሳቱ ሲጠብሰኝ፤
ወላፈን ሲገርፈኝ፤
እንቅልፍ ለምኔ ? ለመቼ ሊሆነኝ ?!
ትኋን ደሜን ሲመጥ፤
ስተኛ ስቀመጥ፤
ቁንጫ ሲበላኝ፤
ቅማል ሲያላምጠኝ፤
እንቅልፍ ለምኔ ? ለመቼ ሊሆነኝ ?!

ውሻ ሲቦጫቅኝ፤
ጅብ ሲሰለቅጠኝ፤
ነብር ሲያፈጥብኝ፤
አህያ ሲረግጠኝ፤
እንቅልፍ ለምኔ ? ተኝቼ ምን ላገኝ !
ሙጃሌ ቦርሳ አርጋው እግሬ ሲውተረተር፤
መጠለያ ሆኖ ብብቴ ለመዥገር፤
እያከኩ ከምኖር፤
ስመጠጥ ከምኖር፤
እምቅልፍ ለምኔ ? ቆሜ ከዞብ ልደር !!

አንጀቴ ሲላወስ ኮሶ ትል ተጣብቶኝ፤
ሳልበላ እንደበላ ቅልሽልሽ ሲያረገኝ፤
ወዘናዬ ጠፍቶ አመድ ተሸከሜ፤
ዊን ዊን እያልኩኝ በደከመ አጥሜ፤
እንቅልፍ ለምኔ ? ልደር እንጂ ቆሜ !
ዝንቦቹ ሲወሩኝ፤
ትንኝ ሲያሾፍብኝ፤
ወባ ሲያስጨፍረኝ፤
እስከታ ሲያስመታኝ፤
በሳቄ አሳዝኖ ባዘኔ ሲያስቀኝ፤
እንቅልፍ ለምኔ ? እንኳንስ ለሥጋ ለንብሴም አልበጀኝ !

EthioLion.Com

EthioLion

*ውሃ ጥም ሲያጋየኝ፤*
*ችጋር በስለቱ ሲያርደኝ ሲያላምጠኝ፤*
*በሽታ በርግጫ በካልቾ ሲለጋኝ፤*
*ብርድና ፀሐዩ ሲፈራረቅብኝ፤*
*እንቅልፍ ለምኔ ? ለመቼ ሊሆነኝ ?!*
*ሰማይ ላይታለብ ምሎ ተገዝቶ፤*
*መሬቷ መክና የሚበቅል ጠፍቶ፤*
*ፀሐይ ፈገግ ላትል ጥቁር ጭንብል ደፍታ፤*
*ጨረቃ እርም ብላ ከሱባኤ ገብታ፤*
*እንቅልፍ ለምኔ ? ማሸለብ መኙታ !*
*እንቅልፍ ለምኔ ? መጋደም መኙታ !*

*አንድ ቀን*

*በችግር ለሚማቅቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ መታሰቢ*

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!